Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት
ኤጀንሲ

THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN INVESTMENT
AGENCY

ቀን 6 መጋቢት 2005
DATE

ቁጥር ኢአ4/16/ዛ
REF.No.

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

ለትግራይ ክልላዊ መንግሥት የከተማ ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ
<u>መቀሌ</u>

ለአፋር ክልላዊ መንግሥት የንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርትና የኢንቨስትመንት ቢሮ
<u>ሠመራ</u>

ለአማራ ክልላዊ መንግሥት የንግድና ኢንዱስትሪ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ቢሮ
<u>ባህርዳር</u>

ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
<u>ሐዋሳ</u>

ለጋምቤላ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
<u>ጋምቤላ</u>

ለሐረሪ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ማዕድንና ኢነርጂ ጽ/ቤት
<u>ሐረሪ</u>

ለቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት
<u>አሶሳ</u>

ለሶማሌ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
<u>ጅግጅጋ</u>

ለአዲስ አበባ የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
<u>አዲስ አበባ</u>

ለድሬደዋ የንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ
<u>ድሬደዋ</u>

ጉዳዩ፡- <u>በአዲስ መልክ ተሻሽሎ የፀደቀውን ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ስለመላክ፤</u>

ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች ባወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 ዓ.ም አንቀጽ 14 መሰረት የኢንቨስትመንት ቦርድ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ አዲስ መመርያ አውጥቷል፡፡

በመሆኑም 28 ገጽ የያዘውን መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን ሲሆን፤መመሪያው ከመጋቢት 4 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ፍፁም አረጋ
ዋና ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለግብርና ሚኒስቴር
- ለትራንስፖርት ሚኒስቴር
- ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
- ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
- ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

ስልክ 011- 551 00 33
Tel. 011-553 72 86
✉ 2313
Website = www. ethioinvest.org
E-mail address = ethiopian.invest@ethioinvest.org
ፋክስ
Fax; 011-551 43 96

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

# የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ

## ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ

## መመሪያ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Agency

መጋቢት 4 ቀን 2005 ዓ.ም

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

# ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ የወጣውን መመሪያ ቍጥር 3/2003 (እንደተሻሻለ) ከአዲሱ የኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቍጥር 769/2004 እና ይህንኑ ደንብ ለማስፈጸም ከወጣው የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቍጥር 270/2005 ጋር አጣጥሞ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቁጥር 769/2004 እና ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቍጥር 270/2005 አንቀጽ 14 መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ - ጠቅላላ

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢንቨስትመንት ቦርድ የወጣ መመሪያ ቍጥር 4/2005 ዓ.ም.›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Investment Agency

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## አንቀጽ 2

## ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ፡-

1) **‹‹ተሽከርካሪ››** የሚለው ቃል የደረቅ፣ የፍሳሽ/የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪናን ወይም ለተለየ አገልግሎት ተብለው የሚዘጋጁ ተመሳሳይ መኪኖችን፤ ፒክ-አፕን፣ ማናቸውም ዓይነት ስቴሽን ዋገንን፣ ከሕዝብ መንገድ ውጭ አገልግሎት የሚሰጥ ልዩ መኪናን (ቶም ካርን) ፣ አውቶቡስን፣ ሚኒባስን፣ ሸፍን የዕቃ ማጓጓዣ መኪናን (ዴሊቨሪ ቫንን) እና ሞተር ብስክሌትን የሚያካትት ነው፡፡

2) **‹‹አውቶቡስ››** ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ቢያንስ 30 መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

3) **‹‹ሚኒባስ››** ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ከ10 ያላነሰ እና ከ15 ያልበለጠ መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

4) **‹‹ፒክአፕ››** ማለት 2WD ወይም 4WD የሆነ፣ የስሊንደሩ ብዛት በአዲስ አበባና በአዲስ አባባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከሆነ ከ4 ያለበለጠ፤በሌሎች አካባቢዎች ከሆነ ከ6 ያልበለጠ እና የመጫን አቅሙ ከ500 ኪ.ግ. እስከ 1500 ኪ.ግ. የሆነ ተሽከርካሪ ነው፡፡

5) **‹‹ዴሊቨሪ ቫን››** ማለት የመጫን አቅሙ ከ3000 ኪ.ግ. እስከ 5000 ኪ.ግ. የሆነ ሸፍን የጭነት ተሽከርካሪ ነው፡፡

6) **‹‹የጭነት መኪና››** ማለት ተሳቢውን ጨምሮ የመጫን አቅሙ ከ5000 ኪ.ግ. በላይ የሆነ ተሽከርካሪ ነው፡፡

7) **‹‹ለተለየ አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ››** ማለት የሥራ መስኩ ልዩ ባህርይ የሚጠይቃቸውና ለመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት የማይውሉ ተሽከርካሪዎች ናቸው፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

8) «ሞተር ብስክሌት» ማለት የሞተር አቅሙ ግምት ውስጥ ሳይገባ ባለሁለት ጎማ ተሽከርካሪ ነው፡፡

9) «ሆቴል»፣ «ሎጅ»፣ «ሬስቶራንት»፣ እና «ሞቴል» በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 173/2002 መሠረት የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

10)«ሪዞርት ሆቴል» ማለት ለመዝናናት፣ የዕረፍት ጊዜን ለማሳለፍ፣ ወዘተ. በሚያስችል መልኩ ከከተማ ወጣ ብሎ በመዝናኛ ሥፍራዎች የሚቋቋም ዘመናዊ ሆቴል ነው፡፡

11)«የኢንዱስትሪ ቀጣና» በኢንቨስትመንት ዓዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

12) «ዓዋጁ» ማለት የኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቁጥር 769/2004 ነው፡፡

13) "ደንብ" ማለት ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 ነው፡፡

14) በኢንቨስትመንት ዓዋጁና ደንቡ ለተለያዩ ቃላትና ሐረጋት የተሰጡ ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው የኢንቨስትመንት መስኮችና የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት

### አንቀጽ 3

### የተሽከርካሪ ማበረታቻ የሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት መስኮች

በዚህ መመሪያ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የማስገባት ማበረታቻ የሚሰጠው በማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ በግብርና፣ በኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት፣ የኮከብ ደረጃ

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

ባላቸው ሆቴሎች (የሪሶርት ሆቴሎችን ጨምሮ)፣ ሞቴሎች፣ ሬስቶራንቶችና ሎጆች፤ በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት፤ በአስጎብኝነት ሥራ እና በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ የሥራ መስኮች አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ለሚያቋቁሙ ወይም ነባር ድርጅታቸውን ለሚያስፋፉ ባለሀብቶች ብቻ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 4

## ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በዚህ መመሪያ በሠንጠረዥ አንድ ከተመለከቱት የሥራ መስኮች በአንዱ ቢያንስ 10 ሚሊዮን ብር ካፒታል ለፕሮጀክቱ የሚያውል ማንኛውም ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲያስገባ የሚፈቀዱለት የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተመለከተው በሥራ መስክ እና በሚቋቋምበት የልማት አካባቢ ይሆናል፡፡

2) ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ለተመለከቱት የማምረቻ ኢንዱስትሪ የኢንቨስትመንት መስኮች ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀደው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Investment Agency

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## ሠንጠረዥ አንድ

## ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀድ ተሽከርካሪዎች በኢንቨስትመንት ሥራ መስክና በአስተዳደር አካባቢዎች

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 1. የምግብ ኢንዱስትሪ<br>1.1. ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን ማቀነባበር<br>1.2. ዓሣና የዓሣ ውጤቶችን ማቀነባበር<br>1.3. ፍራፍሬ እና/ወይም አትክልት ማቀነባበር<br>1.4. የምግብ ዘይት ማምረት<br>1.5. ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ውጤቶችን ማምረት<br>1.6. ስታርች እና የስታርች ውጤቶችን ማምረት<br>1.7. ዱቄትን ማምረት ሳይጨምር ጥራጥሬ፣ የቅባት እህል ወይም ሌላ እህል ማቀነባበር<br>1.8. ሌሎች ምግቦችን ማምረት | አንድ | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 1.9. ስኳር ማምረት | - | - | - | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 1.10. ቸኮሌት፣ ከረሜላ፣ብስኩት ወይም ሌሎች ጣፋጭ ምግቦችን (አይስክሬም፣ጄላቲን እና ኬክን ሳይጨምር) ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| 1.11. ማካሮኒ፣ ፓስታ እና/ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አንድ |
| 1.12. የሕጻናት ምግብና ወተት፣ ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ፣ እርሾ፣ ሆምጣጤ፣ማዮኔዝ፣ሰው ሰራሽ ስኳር፣ አዮዲን የተጨመረበት ጨው፣ ወይም መሰል | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አንድ |

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| ምግቦችን ማምረት | | | | | | |
| 1.13. የእንስሳት መኖ ማቀነባበር | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 2. **የመጠጥ ኢንዱስትሪ**<br>2.1. የአልኮል መጠጥ ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 2.2. የወይን ጠጅ ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 2.3. ቢራ እና/ወይም የቢራ ብቅል ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 2.4. ለስላሳ መጠጥ፣ የማዕድን ወይም የታሸጉ ሌሎች ውኃዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 3. **የጨርቃጨርቅና የስፌት ውጤቶች ኢንዱስትሪ**<br>3.1. የጥጥ፣ የሱፍ፣ የሐር እና የመሳሰሉ የጨርቃጨርቅ ጥሬቶችን ማዘጋጀትና መፍተል | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 3.2. ጨርቃጨርቅ መሸመን (ጨርቃጨርቅ መፍተልንና ማጠናቀቅን ሊጨምር ይችላል) | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 3.3. ጨርቃጨርቅ ማጠናቀቅ<br>3.3.1. ጣቃ ጨርቅ፣ ክር፣ ድርና ማግ፣ አልባሳትና ሌሎች የጨርቃጨርቅ ውጤቶችን ማንጣትን ወይም ማቅለምን ሳይጨምር ጨርቃጨርቅ ማጠናቀቅ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 3.3.2. ሌሎች የጨርቃጨርቅ ማጠናቀቅ ሥራዎች | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 3.4. ሌሎች ጨርቃጨርቆችን ማምረት<br>3.4.1. ሹራብ ወይም ፎጣ ማምረት<br>3.4.2. ከአልባሳት በስተቀር የተዘጋጁ ጨርቃጨርቆችን ማምረት ምንጣፍ ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 3.5. የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትን (የስፖርት አልባሳትን ጨምሮ) ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 3.6. የጨርቃጨርቅ ውጤቶች ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 4. <u>የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u> | | | | | | |
| 4.1. ባለቀለት ደረጃ ቆዳና ሌጦ ማልፋት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 4.2. ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 4.3. የቆዳ ውጤቶችን (ሻንጣ፣ቦርሳ፣የቆዳ ኳስ እና የመሳሰሉትን) ማምረት<br>4.4. የቆዳ ጫማ ማምረት | ሁለት | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት | አንድ |
| 4.5. የቆዳ ውጤቶች ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት |
| 5. የእንጨት ውጤቶችን (እንጨት [illegible]ቅን፣ጣውላ ማምረትን እና [illegible] የተዘጋጁ የእንጨት ውጤቶች[illegible]ገጣጠምን ሳይጨምር) ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 6. **የወረቀት እና የወረቀት ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | - | - | - | ሁለት | – | ሁለት |
| 6.1. ፐልፕ ማምረት | | | | | | |
| 6.2. ወረቀት ማምረት | - | - | - | ሁለት | አንድ | አንድ |
| 6.3. የወረቀት ማሸጊያዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አንድ |
| 6.4. ሌሎች የወረቀት ውጤቶችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| 7. **የማተሚያ ኢንዱስትሪ** | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 8. **የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ** | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት | አንድ | አንድ |
| 8.1. መሠረታዊ ኬሚካሎችን ማምረት | | | | | | |
| 8.2. ማዳበሪያ እና/ወይም የናይትሮጅን ውህዶችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 8.3. የፕላስቲክ እና/ወይም የሰው ሠራሽ ጎማ ጥሬ ዕቃዎችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 8.4. ፀረ-ተባይ፣ ፀረ-አረም ወይም ፀረ-ሻጋታ ማምረት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| 8.5. የግድግዳ ቀለም፣ ቫርኒሽ ወይም መሰል መለሰኛዎችን፣ የማተሚያ፣ የመጻፊያ ወይም የሥዕል ቀለም ወይም ማጣበቂያ ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 8.6. ሳሙናና ዲተርጀንት፣ ማፅጃና መወልወያ፣ ሽቶ እና መሰል መዋቢያዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አንድ |
| 8.7. ሰው ሠራሽ ጭረቶችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 8.8. ሌሎች የኬሚካል ውጤቶችን ( ባሩድ፣ ፈንጂ፣ የፎቶግራፍ ፊልም እና የመሳሰሉትን) ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም |
| 9. <u>የመሠረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ዝግጅት ኢንዱስትሪ</u><br>9.1. ለመድኃኒት ግብዓትነት የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃኒት ውጤቶችን ማምረትና ማዘጋጀት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት | አንድ | አይፈቀድም |
| 9.2. መድኃኒት ማምረት ወይም ማዘጋጀት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት | አንድ | አይፈቀድም |
| 10. <u>የጎማና የፕላስቲክ ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u><br>10.1. የጎማ ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | አንድ |
| 10.2. ለሕንጻ ግንባታ፣ ለተሽከርካሪ ወይም ለሌሎች የኢንዱስትሪ ምርቶች ግብዓት የሚሆኑ፣ ለመስኖና ለመጠጥ ውሃ ማስተላለፊያነት እንዲሁም ለፍሳሽ ማስወገጃ የሚያገለግሉ የፕላስቲክ ቧንቧዎችን ወይም ቱቦዎችን እና መገጣጠሚያዎችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | አንድ |
| 10.3. ፌስታልን ሳይጨምር ሌሎች የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| 11. <u>ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u><br>11.1. መስተዋት እና/ ወይም የመስታወት ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Investment Agency

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 11.2. የሴራሚክ ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 11.3. ሲሚንቶ ማምረት | – | – | – | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 11.4. የሸክላና የሲሚንቶ ውጤቶችን ማምረት | – | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 11.5. ዕብነ በረድ እና የኖራ ድንጋይ መቁረጥ፣ ቅርፅ ማውጣት እና ማጠናቀቅ (የማዕድኑን ሥራ ሳይጨምር) | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 11.6. ኖራ፣ ጀሶ እና/ወይም የመሳሰሉ መለሰኛዎችን ማምረት | – | – | – | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 11.7. የወፍጮ ድንጋይ፣ የብርጭቆ ወረቀት ወይም የድምጽ መገደብያ ወይም የሙቀት መከላከያ ምርቶችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 12. <u>የመሠረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ (የማዕድኑን ሥራ ሳይጨምር)</u><br>12.1. መሠረታዊ ብረትና የአረብ ብረት ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 12.2. መሠረታዊ የከበሩና የብረት ይዘት የሌላቸው ብረታ ብረቶችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 12.3. ከብረት እና ከአረብ ብረት ፈሳሽ የተለያዩ ቅርፃችን ማውጣት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | አንድ |
| 13. <u>የማምረቻ መሣሪያዎችንና ዕቃዎችን ማምረትን የማይጨምር የብረታብረት ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u><br>13.1. የማዋቅሪያ ብረት ውጤቶችን፣ የብረት በርሜሎችን፣ ገንዳዎችን እና [illegible]ነሮችን ወይም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| የእንፋሎት ማመንጫዎችን ማምረት | | | | | | |
| 13.2. የቤት ክዳን ቆርቆሮ እና ምስማርን ሳይጨምር ሌሎች የብረታ ብረት ውጤቶችን (የእጅ መሣሪያ፣ ቁሳቁስ እና የመሳሰሉትን) ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 14. **የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ**<br>14.1. የኤሌክትሮኒክስ አካሎችንና ስሌዳዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| 14.2. ኮምፒዩተር እና ተጓዳኝ ዕቃዎችን ማምረት<br>14.3. የመገናኛ መሣሪያዎችን ማምረት<br>14.4. የፍጆታ ኤሌክትሮኒክስ (ቴሌቪዥን፣ ዲ.ቪ.ዲ፣ ሬድዮ እና የመሳሰሉ) ዕቃዎችን ማምረት<br>14.5. የመለኪያ፣ የመፈተሻ፣ የመቃኛ፣ የመቆጣጠሪያ ዕቃዎችን ወይም ሰዓት ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 14.6. የሕክምና መሣሪያዎችን (ኢራዲዬሽን፣ ኤሌክትሮ-ሜዲካል ወይም ኤሌክትሮ - ቴራፔቲክ) ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 14.7. የዕይታ ወይም የፎቶ ማንሻ ዕቃዎችን ማምረት<br>14.8. መግነጢሳዊ እና የዕይታ ሚዲያዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 15. <u>የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u><br>15.1. የኤሌክትሪክ ሞተር፣ ጀነሬተር፣ ትራንስፎርመር ወይም የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ወይም መቆጣጠሪያ ዕቃዎችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 15.2. የኤሌክትሪክ ኃይል ማከማቻ ወይም ባትሪ ማምረት<br>15.3. የኤሌክትሪክ ኃይል ሽቦዎችን ወይም ገመዶችን (የፋይበር ኦፕቲክስን ጨምሮ) እና ተያያዥ ዕቃዎችን ማምረት<br>15.4. የኤሌክትሪክ ብርሃን መስጫ ዕቃዎችን ማምረት<br>15.5. የቤት ውስጥ መገልገያ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ማምረት፣<br>15.6. ሌሎች የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 16. <u>የማምረቻ /አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u><br>16.1. ሁለገብ መሣሪያዎችን (ሞተር፣ ዕቃ ማንሻ፣ ፓምፕ እና የመሳሰሉትን) ማምረት<br>16.2. ለተለያዩ ዓላማዎች (ለግብርና ሥራ፣ ለምግብ ማቀነባበሪያ፣ [illegible]ጣጥ፣ ለጨርቃ ጨርቅና [illegible] ለማምረት የሚሆኑና [illegible] ሥራዎች) የሚውሉ መሣሪያዎችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 17. የመኪና፣ የተጎታች እና ከፊል ተጎታች ኢንዱስትሪ<br>17.1. መኪና ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.2. የመኪና አካላትን፣ ተጎታችን እና/ወይም ከፊል ተጎታችን ማምረት፣<br>17.3. የመኪና መለዋወጫዎችን እና ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.4. የባቡር ሞተሮችን (locomotives) እና ጋሪዎችን ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.5. ሌሎች የትራንስፖርት ዕቃዎችን (ጀልባ፣ ብስክሌት፣ ሞተር ብስክሌት እና የመሳሰሉትን) ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 18. የቢሮና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን (ከሴራሚክ የሚሠሩትን ሳይጨምር) ማምረት | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 19. ሌሎች ዕቃዎችን (የጌጣጌጥና ተዛማጅ ዕቃዎች፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ የስፖርት ዕቃዎች፣ መ[illegible]ቻዎችና አሻንጉሊቶች እና የመሳሰሉትን) ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| 20. ከግብርና ጋር የተቀናጀ የማምረቻ ኢንዱስትሪ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 21. ከግብርና ጋር [illegible]ተቀናጀ የማምረቻ ኢንዱስትሪ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

3) በዚህ መመሪያ ባሠንጠረዥ አንድ ከተዘረዘሩት የማምረቻ ኢንዱስትሪ የኢንቨስትመንት መስኮች መካከል በአንዱ ለሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ፡-

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ (የፋብሪካ ሕንፃ ተከራይቶም ከሆነ ሕጋዊ የኪራይ ውል) ማስረጃ፣

ለ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት ፣ መሠረተ-ልማት፣ መጋዘን፣ መንገድ እና የመሳሰሉት ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ካለበት የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ማስረጃ፣

ሐ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ አገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግገር ደረሰኝ (Invoice) ወይም የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግገርውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣

መ/ ባለሀብቱ የፋብሪካ ሕንፃ ተከራይቶ የሚሠራ ከሆነ የመሣሪያ ተከላ ስለመጀመሩ ፕሮጀክቱ ካለበት የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ማስረጃ፣ እና

ሠ/ በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ (bank statement)፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከፊደል ተራ ‹ሀ› እስከ ‹ሠ› የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለሀብት ከፒክ-አፕ እና ሞተር ብስክሌት በስተቀር ሌሎቹን ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የሙከራ ምርት ማምረት [illegible] አግባብ ካለው አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መ[illegible]ብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

5) ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የማምረት ሥራ ሲጀምር ለኢንቨስትመንቱ ያዋለው የካፒታል መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት የተሟላ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለፈቀደው አካል ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ የካፒታል መጠኑ ከተመለከተው በታች ሆኖ ከተገኘ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ላስገባው/ቸው ተሽከርካሪ/ዎች ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

<u>አንቀጽ 5</u>

<u>ለግብርና ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች</u>

1) በዚህ መመሪያ በሠንጠረዥ ሁለት ከተመለከቱት የሥራ መስኮች ቢያንስ በአንዱ ለሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲያስገባ የሚፈቀዱለት ተሽከርካሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) በተገለፀው መሠረት በሚያለማው የመሬት ሥፋት፣ በሚኖረው የእንስሣት ብዛት፣ የቀፎ ብዛት ፣ የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት ወይም ለፕሮጀክቱ ባዋለው የመሬት ሥፋት ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሀብቱ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት፣

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ ወይም ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፣

ለ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ መሠረተ ልማት ፣ መጋዘን፣ መንገድ እና የመሣሠሉት ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት ክልል የኢንቨስትመንት መ/ቤት የተሰጠው ማስረጃ፣ እና

ሐ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመገዛታቸው ቢል ኦፍ ሊዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግገር ደረሰኝ (Invoice)፣ ወይም

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Agency

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

መ/ የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግገርውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከፊደል ተራ 'ሀ' እስከ 'መ' የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ባለሀብት ከፒክ-አፕ፣ የጭነት መኪና እና ሞተር ብስክሌት በስተቀር ሌሎቹን ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የሙከራ ምርት ማምረት ስለመጀመሩ አግባብ ካለው አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

4) ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የማምረት ሥራ ሲጀምር ያለማው የመሬት ስፋት ወይም ያለው የእንስሳት ብዛት ወይም የቀፎ ብዛት ወይም የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት ወይም ለፕሮጀክቱ ያዋለው የመሬት ሥፋት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተው መጠን የተሟላ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለፈቀደው አካል ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ መጠኑ ከተመለከተው በታች ሆኖ ከተገኘ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ላስገባው/ቸው ተሽከርካሪ/ዎች ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

5) ለእርሻ ልማት ኢንቨስትመንት ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Agency

## ሠንጠረዥ ሁለት

### ለግብርና ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀድ ተሽከርካሪዎች በኢንቨስትመንት ሥራ መስክና በአስተዳደር አካባቢዎች

| ግብርና | የማለማው መሬት ስፋት(በሄክታር) | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያየኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ፒክ አፕ መኪና | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና |
| 1. የእርሻ ልማት | | | | | | | |
| 1.1. የዓመታዊ ሰብሎች ልማት | | | | | | | |
| 1.1.1. የብርዕ፣ የአገዳ፣ የጥራጥሬ እና/ወይም የቅባት እህሎች እና ሩዝ ማምረት | 200-300 | - | - | - | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| | ከ300 በላይ -1000 | - | - | - | ሁለት | ሁለት | አንድ |
| | ከ1000 በላይ-2000 | - | - | - | ሁለት | ሶስት | ሁለት |
| 1.1.2. የጭረት ሰብሎችን ማምረት | ከ2000 በላይ-3000 | - | - | - | ሦስት | አረት | ሶስት |
| | ከ3000 በላይ-4000 | - | - | - | አራት | አምስት | አራት |
| 1.1.3. የእንስሳት መኖ ማምረት | ከ5000 በላይ | - | - | - | አምስት | ስድስት | አምስት |
| 1.1.4. አትክልት ማምረት | ከ50-100 | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| | ከ100 በላይ | ሁለት | አይፈቀድም | አይፈቀድም | ሁለት | አንድ | አይፈቀድም |
| 1.1.5. ሌሎች ዓመታዊ ሰብሎችን (ለመድኃኒትነት፣ ለሽቶ ፣ለጣዕምነት/ ለቅመም ነት እና ለመሳሰሉት የሚሆኑ ምርቶችን) ማምረት | ከ10-30 | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| | ከ30 በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| 1.1.6. የተረጋገጠ ምርጥ ዘር ማምረት | ከ50 በላይ | - | - | - | አንድ | አንድ | አንድ |
| 1.2. የመካከለኛ ጊዜ ቋሚ ተክሎች ልማት | | | | | | | |
| 1.2.1. የአበባ ልማት | ከ10-30 | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| | ከ30 በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| 1.2.2. የመካከለኛ ጊዜ ፍራፍሬዎች (ስትሮቤሪ፣ ብሉቤሪ እና መሳሰሉት) ልማት | ከ50-100 | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| | ከ100 በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |

| ግብርና | የፕሮጀክት አቅም በእንስሳት ብዛት፣በቀፎ ብዛት ፣ በሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት ወይም በመሬት ስፋት | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ፒክ አፕ መኪና | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና |
| **2. የእንስሳት ሀብት ልማት** | | | | | | | |
| 2.1. የቤት እንስሳት እና ተዋጽኦ ልማት | | | | | | | |
| 2.1.1. የዶሮ እና የመሳሰሉ አእዋፋት እርባታና ተዋጽኦ ልማት | 2,000-10,000 | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| | ከ10,000 በላይ - 50,000 | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | አንድ |
| | ከ50,000 በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 2.1.2. የበግ፣የፍየል እና አሳማ እርባታና ተዋጽኦ ልማት | ከ500-1,000 | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| | ከ1,000 በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 2.1.3. የቀንድና የጋማ ከብት እርባታና ተዋጽኦ ልማት ( ግመልን ጨምሮ)፣ | ከ200-500 | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| | ከ500 በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 2.2. የዱር እንስሳት እና ተዋጽኦ ልማት | | | | | | | |
| 2.2.1. የጅግራ፣የቆቅና የመሳሰሉ አእዋፋት እርባታና ተዋጽኦ ልማት | ከ1,000-5,000 | – | – | – | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| | ከ5,000 በላይ-10,000 | – | – | – | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| | ከ10,000 በላይ | – | – | – | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 2.2.2. የሰጎን እርባታና ተዋጽኦ ልማት | ከ25-50 | – | – | – | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| | ከ50 በላይ-100 | – | – | – | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| | ከ100 በላይ | – | – | – | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 2.2.3. የአዞ እርባታና ተዋጽኦ ልማት | ከ250-500 | – | – | – | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| | ከ500በላይ | – | – | – | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 2.2.4. የጥንቸል እርባታና ተዋጽኦ ልማት | ከ500-1,000 | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| | ከ1,000 በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 2.2.5. የጥርኝ እርባታና ተዋጽኦ ልማት | ከ50-100 | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| | ከ100በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| 2.2.6. ንብ ማነብ/ማር ማምረት | 1,000ቀፎና በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 2.2.7. ሐር ማምረት | ከአንድ ሄክታር በላይ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| 2.2.8. በሰው ሠራሽ ኩሬ ዓሣ ማምረት | 1250ሜ.ኩ.እና በላይ | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አይፈቀድም |

21



Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## አንቀጽ 6

## ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ በመክፈል ለማስገባት የሚፈቀድለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው መሠረት ነው::

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው የሥራ መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብቱ፡-

   ሀ/ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ወይም የሚመለከተው ሌላ የመንግሥት አካል ለየደረጃው እንደሚያስፈልጉ ከዘረዘራቸው መሣሪያዎች በዋጋ 25% ያህሉን ከውጭ አገር ስለመግዛቱ ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግገር ደረሰኝ (Invoice) ወይም ሌላ የዋጋ ግምት ማረጋገጫ ሠነድ ፤ ወይም

   ለ/ መሣሪያዎቹን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግገር ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች ጋር፣

   የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው::

3) ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱ የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል::

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## ሠንጠረዥ ሦስት

## ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት ሥራዎች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በኢንቨስትመንት ሥራ መስክና በተቋራጭነት ደረጃ

| ተራ ቁጥር | የኮንስትራክሽን ዘርፍ | ደረጃ አንድ | ደረጃ ሁለት | ደረጃ ሦስት | ደረጃ አራት | ደረጃ አምስት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት | | | | | |
| | 1.1. ፒክ አፕ | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | 1.2. የጭነት መኪና | - | - | - | - | - |
| | 1.3. የውኃ መያዣ የተገጠመለት መኪና | 1 | 1 | - | - | - |
| | 1.4. የውኃ መርጫ የተገጠመለት መኪና | 1 | 1 | - | - | - |
| 2. | የሕንፃ ሥራ ተቋራጭነት | | | - | - | - |
| | 2.1. ፒክ አፕ | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | 2.2. የጭነት መኪና | - | - | - | - | - |
| | 2.3. የውኃ መያዣ የተገጠመለት መኪና | 2 | 1 | - | - | - |
| 3. | የመንገድ ሥራ ተቋራጭነት | | | | | |
| | 3.1. ፒክ አፕ | 2 | 1 | 1 | 1 | - |
| | 3.2. የውኃ መያዣ የተገጠመለት መኪና | 1 | 1 | - | - | - |
| | 3.3. የውኃ መርጫ የተገጠመለት መኪና | 2 | 1 | - | - | - |
| 4. | ልዩ ሥራ ተቋራጭነት (ለኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ብቻ) | | | | | |
| | 4.1. ፒክ አፕ | 1 | 1 | - | - | - |
| | 4.2. የጭነት መኪና | - | - | - | - | - |
| 5. | የውኃ ሥራ ኮንስትራክሽን ተቋራጭነት | | | | | |
| | 5.1. የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ | ለአንድ ድሪሊንግ ሪግ 1 ፒክ አፕ ፣ 1 ክሬን ትራክ እና 1 የጭነት መኪና፣ ሆኖም የሚፈቀደው ፒክ አፕ ብዛት ከ4 መብለጥ የለበትም፡፡ | | | | |
| | 5.2. ሌላ የውኃ ሥራ ኮንስትራክሽን ተቋራጭነት | 2 | 1 | - | - | - |
| 6. | የመሠረት ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታ ሥራ ተቋራጭነት | ለአንድ መቆፈሪያ/መሰርሰሪያ መሣሪያ 1 ፒክ አፕ ፣ 1 ክሬን ትራክ እና 1 የጭነት መኪና፣ ሆኖም የሚፈቀደው ፒክ አፕ ብዛት ከ4 መብለጥ የለበትም፡፡ | | | | |
| 7. | የማዕድን ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተቋራጭነት | ለአንድ ድሪሊንግ ሪግ 1 ፒክ አፕ ፣ 1 ክሬን ትራክ እና 1የጭነት መኪና፣ ሆኖም የሚፈቀደው ፒክ አፕ ብዛት ከ4 መብለጥ የለበትም፡፡ | | | | |

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## አንቀጽ 7

## የኮከብ ደረጃ ላላቸው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንትና የሎጅ አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) የኮከብ ደረጃ ባለው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንት ወይም የሎጅ አገልግሎት የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሚያወጣውን የደረጃ መሥፈርት መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ አኳኋን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ተሽከርካሪዎችን ከውጭ ማስገባት ይችላል፡፡

### ሠንጠረዥ አራት

### የኮከብ ደረጃ ላላቸው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንትና የሎጅ አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በኮከብ ደረጃ

| ተ.ቁ. | የኮከብ ደረጃ | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | 1 ወይም 2 | 1 ፒክ አፕ |
| 2. | 3 ወይም በላይ | 2 ፒክ አፕ |

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገባ በባለሀብት ሲጠየቅ፦

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ ማስረጃ፣ እና

ለ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የሕንፃው ግንባታ፣ መሠረተ-ልማት እና መጋዘን የመሳሰሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ማስረጃ

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም እንደ አግባቡ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## አንቀጽ 8

## ለመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

በኢንቨስትመንት ቦርድ በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2001 መሠረት ማበረታቻ የሚፈቀድለት ማንኛውም በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት ኢንቨስትመንት መስክ የተሠማራ ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ዴሊቨሪ ቫን ከውጭ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡ ሆኖም የሚያስገባው ዴሊቨሪ ቫን ብዛት ከ3 አይበልጥም፡፡

## አንቀጽ 9

## ለአስጎብኝነት አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በአስጎብኝነት ኢንቨስትመንት መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት 3 አዳዲስ ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪዎችን በአንድ ዓመት ውስጥ በሁለት ጊዜ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአስጎብኝነት የሥራ መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት አንድ አውቶቡስ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሠረት ተሽከርካሪዎቹን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ፦

ሀ/ የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ያወጣውን መሥፈርት በማሟላት አግባብ ካለው አካል የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ አውጥቶ/አግኝቶ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ወይም ወደ ኢንቨስትመንት መስኩ የሚሠማራ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ/ ተሽከርካሪዎቹ አዳዲስ ስለመሆናቸው ከተፈበረኩበት/ባቸው ፋብሪካ/ዎች ወይም ከአቅራቢዎች ማስረጃ ማቅረብ እና ተሽከርካሪዎቹን ለማስጎብኘት ሥራ ብቻ እንደሚያውላቸው በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ፊት ቀርቦ ግዴታ መግባት ይኖርበታል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Agency

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሠረት ለአስጎብኝነት ሥራ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ለመለየት በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በሚወሰነው መሠረት የመለያ ምልክት እንዲኖራቸው ይደረጋል፤ ተሽከርካሪዎቹ ለተፈቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውንም እንዲቆጣጠርና እንዲያረጋግጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## አንቀጽ 10

## ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

3) በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ የሥራ መስክ የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ አኳኋን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ተሽከርካሪዎችን ከውጭ ማስገባት ይችላል፡፡

### ሠንጠረዥ አምስት

### ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

| ተ.ቁ. | የማመንጨት አቅም | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | እስከ 50 ሜ.ጋ ዋት | 2 ፒክ አፕ እና 2 የጭነት መኪና |
| 2. | ከ50 ሜ.ጋዋት በላይ - 100 ሜ.ጋ ዋት | 2 ፒክ አፕ እና 3 የጭነት መኪና |
| 3. | ከ100 ሜ.ጋዋት በላይ - 150 ሜ.ጋ ዋት | 3 ፒክ አፕ እና 3 የጭነት መኪና |
| 4. | ከ150ሜ.ጋዋት በላይ | 3 ፒክ አፕ እና 4 የጭነት መኪና |

## አንቀጽ 11

## የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች

1) በአስጎብኝነት ኢንቨስትመንት ሥራ መስኮች ላይ የሚሠማሩትን ሳይጨምር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 በተመለከቱት የኢንቨስትመንት መስኮች የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ለሠራተኛ ማጓጓዣ የሚያስፈልገውን ተሽከርካሪ እንደ ፕሮጀክቱ የሠራተኛ ብዛት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ በቅድሚያ፣

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ/ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፣

ለ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ አገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Track-way Bill) እና የግገር ደረሰኝ (Invoice)፣ ወይም

ሐ/ የካፒታል ዕቃዎቹ ከአገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግገር ውል ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር፣

መ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ የሕንፃ ግንባታ፣ መሠረተ-ልማት፣ መጋዘን እና መንገድ የመሳሰሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት የክልል ኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ማስረጃ፣ እና

ሠ/ ለፕሮጀክቱ በቋሚነት ተቀጥረው በመሥራት ላይ የሚገኙ ሠራተኞችን ሥም ዝርዝር የያዘ ቢያንስ የሦስት ወር የደመወዝ መክፈያ ሰነድ (Pay-roll) እና ለመንግሥት የደመወዝ ግብር የተከፈለበት ማስረጃ

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቀድው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

<u>ሠንጠረዥ ስድስት</u>

<u>ለሠራተኛ ማጓጓዣ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በቋሚ ሠራተኛ ብዛት</u>

| ቋሚ የሠራተኛ ብዛት | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|
| ከ25 - 50 | 2 ሚኒባስ ወይም 1 አውቶቡስ |
| ከ50 በላይ | 3 ሚኒባስ ወይም 2 አውቶቡስ |

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## አንቀጽ 12

## ለተለየ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለማስገባት

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(1) እና 5(1) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ከላይ በሠንጠረዥ አንድ እና ሁለት ከተመለከቱት የሥራ መስኮች መካከል በአንዱ የተሠማራ ባለሀብት እንደተሠማራበት ፕሮጀክት ባህርይ እየታየ ማቀዝቀዣ የተገጠመለት ተሽከርካሪ ወይም ለእንስሳት ማጓጓዣ የሚውል ልዩ ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡ ሆኖም ለአንድ ፕሮጀክት የሚፈቀደው ማቀዝቀዣ የተገጠመለት ተሽከርካሪ ወይም ለእንስሳት ማጓጓዣ የሚውል ልዩ ተሽከርካሪ ብዛት ከ3 አይበልጥም፡፡

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(1) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም አግባብነት ያለው ማናቸውም የማምረቻ ኢንዱስትሪ አንድ የፍሳሽ/የዝቃጭ ማስወገጃ ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

3) በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 3 በተመለከቱት የሥራ መስኮች የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ለሠራተኞች የአደጋ ጊዜ አገልግሎት የሚውሉ አምቡላንሶችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል።

4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(1) እና 5(1) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ከላይ በሠንጠረዥ አንድ እና ሁለት ከተመለከቱት የሥራ መስኮች መካከል በአንዱ የተሠማራ ባለሀብት ቢያንስ 200 ሚሊዮን ብር ኢንቨስት የሚያደርግና ከሚያመርተው ምርት ቢያንስ 60%ም የሚሆነውን ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ እንግዳ ለመቀበልና ፕሮጀክቱን ለማስጎብኘት የሚያስፈልገውን ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይፈቀድለታል። ሆኖም ለአንድ ፕሮጀክት የሚፈቀደው ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪ ብዛት ከሁለት አይበልጥም፡፡

5) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) አፈጻጸም ባለሀብቱ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ምርቱን ወደ ውጭ እየላከ ስለመቆየቱ እና ተሽከርካሪውን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

እንዲገባለት ጥያቄውን ባቀረበበት ወቅት ምርቱን ወደ ውጭ እየላከ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 13

### በአገር ውስጥ ስለሚገጣጠሙ/ስለሚመረቱ ተሽከርካሪዎች

ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብት ከአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ/ማምረቻ ፋብሪካ ተሽከርካሪ ሲገዛ ተሽከርካሪውን ለማምረት ከውጭ ተገዝተው በገቡ የተሽከርካሪው ግብዓቶች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተሠልቶ ይቀነስለታል፡፡

### አንቀጽ 14

### የማስፋፊያ/የማሻሻያ ኢንቨስትመንቶች

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 3 ከተዘረዘሩት ኢንቨስትመንት መስኮች መካከል በአንዱ የተሠማራ እና በኢንቨስትመንት ዓዋጁ መሠረት ነባር ድርጅቱን ያስፋፋ/ያሻሻለ ባለሀብት ለማስፋፊያ/ለማሻሻያ ፕሮጀክቱ በአንቀጽ 4፣ 5፣ 10፣ 11 እና እንደአግባቡ በአንቀጽ 12 ከተመለከቱት የተሽከሪካሪ ዓይነቶች አንዳንድ ተሽከርካሪ በነዚሁ አንቀጾች በተደነገገው መሠረት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

### አንቀጽ 15

### መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንዳስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Agency

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## አንቀጽ 16

## የተሻረ መመሪያ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ድንጋጌዎች

1) ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2003 (እንደተሻሻለ) ተሽሯል፡፡

2) በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት የኢንቨስትመንት መስክ ከገቢ ግብርና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ የሚሰጥባቸው የሥራ መስኮችና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚገቡ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን ዓይነት ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2001 አንቀፅ 5 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

3) ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ተፈጻሚነት የለውም፡፡

## አንቀጽ 17

## የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

የዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ድንጋጌ ቢኖርም ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈቀዱ የተሽከርካሪ ማበረታቻዎችን በሚመለከት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2003 (እንደተሻሻለ) ተፈጻሚነት ይቀጥላል፡፡

ይህ መመሪያ ከ ሚያዚያ 4 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል

አዲስ አበባ

መክንን ማንያዘዋል
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ
ሰብሳቢ

-----------------------------------

የኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features